# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 43 መጋቢት 3 2001 ዓ.ም


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

**...ስለወያኔ ክፋትና ጥፋት፣ በሃገርና በወገን ላይ ስለፈጸመው ወንጀል... የማያውቅ አለ ...?**

**አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በጀርመን ፍራንክፈርት ከኢትዮጵያውያን ጋር ያደረጉት ስብሰባ**

**ገጽ 3 ላይ ይመልከቱ**

## በኢትዮጵያ ቴሌኮሚንከሽን ባለስልጣን ዘረፋው ተጧጡፏል

አንድ የቴሌኮሚኒኬሽን ባለሥልጣን ዜድቲ ከተባለ የቴልኮም ኩባንያ ሀላፊዎች ጋር በመመሳጠር 3 ሚሊዮን ዶላር የኢትዮድያ ቴሌኮሚኒኬሽንን ገንዘብ መመዝበሩን የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ።እንደ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ዘገባ በሙስናው በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ የሚሰሩ ሀላፊዎች ሳይቀሩ እንደተካፈሉበት ገልጸዋል።የቴሌኮሚ ኒኬሽኑ ሀላፊ ዜድቲ ከተባለው ኩባንያ ሀላፊዎች ጋር ሲመሳጠር በቴፕ የተቀዳ ማስረጃ ቢኖርም ለይስሙላ ፍርድ ቤት ቀርቦ ከጥቂት ቀናት በሓላ መለቀቁ ታውቋል።

የኢትዮድያ ቴሌኮሚኒኬሽንን በቻይና መንግስት ባለቤትነት ስር ባለው ዜድቲ በተባለ ኩባንያ ቁጥጥር ለማስገባት የታቀደው ከሞላ ጎደል እንደተሳካ ታውቋል።ይህ በስራ ችሎታው እና በሚያቀርባቸው እቃዎች ጥራት ጉድለት የሚታወቀው ኩባንያ ያለምንም ጨረታ የ1.5 ቢሊዮን ፕሮጀክት ተሰጥቶ እንደነበር የሚታወስ ነው።
ዜድቲ የቴሌኮሚኒኬሽን እቃዎችን ከማቅረብ አልፎ በቅርብ የኢትዮድያ ቴሌኮሚኒኬሽን እና ኢንፎርሜሽን ማሰልጠኛ ማእከልን ለመቆጣጠር መብቃቱ ተዘግቧል።ቴሌኮሚኒኬሽንን ቻይናዊ ለማድረግ በተያዘው ሩጫ ይሄው ዜድቲ የተባለ ኩባንያ እርዳታ ሰጥቻለሁ እና የማሰልጠኛ ተቋሙ ስም ለውጡ ብሎ ተቋሙ ከኢትዮድያ ቴሌኮሚኒኬሽን እና ኢንፎርሜሽ ተቋምነት ወደ ኮሌጅ ኦፍ ቴሌኮሚኒኬሽን ኤንድ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስሙ እንዲቀየር መገደዱን የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ገልጸዋል።

**(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## የግለሰቦች እንግልት በሂልተን

አምባገነኑ መለስ ዜናዊ በድንገት ሂልተን ሆቴል ቅጽር ጊቢ ጃካራንዳ በመባል በሚታወቀው ከመዋኛ ስፍራው አጠገብ ያለ አካባቢ በመምጣቱ በስፍራው የነበሩ የሆቴሉ ሰራተኞች እና በመዝናናት ላይ የነበሩ ሰዎች ለአንድ ሰአት ገደማ ከእገታ ባልተለየ ሁኔታ በጥብቅ ቅጥጥር ስር ውለው እንደነበር ታወቀ። የግንቦት 7 የአዲስ አበባ ዘጋቢ የሆቴሉን ሰራተኞች ጠቅሶ እንደዘገበው መለስ ዜናዊ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው ጃካራንዳ የተባለው ስፍራ የመጣው። በመዝናኛው ስፍራ ሲዝናና የነበረን አንድ ታዋቂ የ አይ ኤም ኤፍ ኤኮኖሚስት ለአንድ ሰአት ገደማ ሲያነጋግር የታየው መለስ የመሰላቸት ስሜት ይነበብበት እንደነበር ተገልጿል። ወያኔ ፈጽሞ መቋቋም ያቃተውን የዋጋ ግሽበት እና የኢኮኖሚ መናጋት ለመቆጣጣር የማይፈነቅለው ድንጋይ ባይኖርም ሁኔታዎቹ ግን ከመሻሻል እየባሰበት እንደሄደ ይታወቃል።

የመለስ በስፍራው መገኘት በጭራሽ ያልተጠበቀ ነበር ያሉት የሆቴሉ ሰራተኞች የሰውየው መምጣት የነሱንም ሆነ የተስተናጋጁን ደስታ እንደቀማ እና ፍጹም ፍርሀት ውስጥ ከቷቸው እንደነበር ለዘጋቢያችን ተናግረዋል። አንድ ለረጅም ጊዜ በሆቴሉ ያገለገለች አስተናጋጅ <<ይሄ ሁሉ ለአንድ ነፍስ ነው? በህይወቴ እንደዚህ ያለ ጥበቃ እና ፍርሀት አይቼ አላውቅም። ለተስተናጋጆች እንኳን መጠጥ ስንቀዳ የመለስ ጠባቂዎች ይገላምጡን ነበር>> ብላለች።አብዛኛው ተስተናጋጅ መውጣትም ሆነ መንቀሳቀስ ተከልክሎ መቀመጫው ላይ ይንቆራጠጥ እንደነበር ታውቋል። ዘረኛ አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ወደ ቦሌ ባለፈ ባገደመ ቁጥር የአዲስ አበባ ነዋሪ እንደ ቆሻሻ ጥራጊ ከየመንገዱ እየተለቃቀመ እንደሚጣል የሚታወቅ ነው።

ዘረኛ አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ወደ ቦሌ ባለፈ ባገደመ ቁጥር የአዲስ አበባ ነዋሪ እንደ ቆሻሻ ጥራጊ ከየመንገዱ እየተለቃቀመ እንደሚጣል የሚታወቅ ነው። በጉዳዩ ዙሪያ ያነጋገርናቸው አንድ ታዛቢ<<መለስ እንኳን መንገድ ሲያልፍ አውሮፕላን ላይ ሲወጣ እንኳን በሩጫ ነው። ፍርሀቱ ወሰን የለውም። እርግጥ ነው በእሱ የጭካኔ እና አረመኔያዊ ትእዛዝ የተቀጠፉ ንጹሀን ደም ዘወትር እያቃዠው ነው የሚንቀለቀው።>> የሚል አስያየታቸውን ሰጥተዋል።

**(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## ውጊያው ተጧጡፏል- 80 የወያኔ ወታደሮች መገደላቸው ተገለጸ

አለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሃን በትናንትናው ዕለት የኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር ያወጣውን መግለጫ ጠቅሰው ግንባሩ ከወያኔ ሰራዊት ጋር ባደረገው ውጊያ ከ80 በላይ የወያኔ ወታደሮችን ገድሎ የሙሽታሂልን ከተማ በቁጥጥሩ ሥር አንዳዋለና በአቅራቢያው የሚገኙትን የዋርደርና የቀላፎ ከተሞችን ለመቆጣጠር በከፍተኛ ውጊያ ላይ እንደሚገኝ ዘገቡ።

የታላቋ ብሪታኒያ ዜና ተቋም የሆነው ቢቢሲ ያነጋገረው አንድ የወያኔ አፈቀላጤ በተለመደው የወያኔ ቅጥፈት ዜናውን ያስተባበለ ሲሆን፤ ከሱማሊያ የሚተላለፈው ሬዲዮ ጋሮዌ ግን የመለስ አገዛዝ በበርካታ ወታደራዊ ካሚዮኖች ተጨማሪ ጦር ወደስፍራው እያጓጓዘ መሆኑንና በአማጽያኑ ቁጥጥር ሥር ከወደቀቺው የሙሽታሂል ከተማ ወደ ፈር ፈር የሚወስደውን አውራ ጎዳና በመዝጋት ከጦርነቱ የሚሸሹ ስቪሎችን ጭምር እንዳገተ አጋልጦአል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፥ አንዱን ብሄር ከሌላው አያጋጨ ዞር ብሎ ደግሞ የብሄር በሔረሰቦችን እኩልነት አረጋግጫለሁ እያለ መቀለድን ለምዷል። ከአገሪቱ አጠቃላይ ነዋሪ ከ15 በመቶ የሚገመተው በረሃብ አለንጋ እየተጠበሰ እስትንፋሱን ለማቆየት የአለም አቀፍ ምግብ እርዳታ በሚጠብቅበት ህብረተሰብ ውስጥ አርሶ አደሩ የሚያመርተው የእህል ምርት አድጎ ብዙዎቹን ሚሊዮነር አድርጌያለሁ በማለትም ተሳልቋል። ከ50 ከመቶ በላይ ሥራ አጥ ባለበት አገር በየአመቱ ከ11 % በላይ የኢኮኖሚ ዕድገት በተከታታይ በማስመዝገብ በአፍሪካ አቻ የሌለኝ የልማት መንግሥት ሆኛለሁ፤...ወዘተ እያለም ያላግጣል። ሰብዓዊ መብቱ ይከበርለት ዘንድ የሚጠይቀውንና በራሱ ክልል መለስና በረከት የሚሾሙለት በአስተሳሰባቸውና በአመለካከታቸው የቀጨጩ ታማኝ አሽከሮች ሳይሆን እራሱ በሚመርጠው ለመተዳደር የሚፈልገውን ህዝብም የተለያየ ቅጽል ሥም በመስጠት በጠላትነት ማሰር፣ መግደልና ከአገር ማሰደድን ሙያ አድርጎ እንደተያያዘው ይህም ለመብቱና ለነፃነቱ ተቆርቋሪ የሆነን ሁሉ መሣሪያ በማንሳት ለመፋለም እንዳነሳሳውና በኦጋዴን ወያኔን እየገጠመው ያለው ሽንፈት የመጨረሻው መጀመሪያ እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በአንድ ወቅት በሰጡት መግለጫ የወያኔ የሃይል ጡንቻ በባዶ እጃቸው ሰላማዊ ትግል በሚያካሂዱት ላይ ብቻ የሚበረታ የፈሪ ዱላ እንደሆነና የተደራጀ በመሳሪያ እራሱን የሚከላከል ትግል ከገጠመው ተሸናፊነቱ የማያጠራጥር እንደሆነ እጽንኦት ሰጥተው እንደተናገሩ የሚታውስ ነው።

## በጸረ ሽብርተኝነት ስም አፋኝ ህግ ሊወጣ ዝግጅቱ መጠናቀቁ ተገለጸ

ወያኔ ሽብረተኛነትን ለመከላከል በሚል ሰበብ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን እና ዜጎችን የሚያስረበት እና የሚያነገላታበት ረቂቅ ህግ ለፓርላማ ተብየው ለማቅረብ በዝግጅት ላይ እንደሆነ የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ አስታውቋል። በቅርቡ በፓርላማ ተብዬው እንደሚቀርብ እና እንደተለመደው ሳይጠየቁ አለቆቻቸውን አይተው በሚንጠለጠሉ እጆች እንደሚጸድቅ የሚጠበቀው ይህ ረቂቅ ህግ በርካታ የዜጎችን መብቶች የሚጥሱ አንቀጾች እንዳሉበት ታውቋል። የረቂቅ ህጉ አንቀጽ አስራ አራት መረጃ ስለመሰብሰብ በሚለው ንኡስ አንቀጽ « ሀ » ስር የደህንነት ሰራተኛ የአንድ ሰው የስልክ፤የሬድዮ፤የፓስታ፤የኢንተርኔት እና የመሳሰሉትን መጥለፍ እና መከታተል እንደሚችል ሲደነግግ ክፍል « ለ » ደግሞ ጠለፋውን ለማስፈጸም ወደ ማንኛውም ቤት ውስጥ በሚስጢር መግባት ወይም በ « ሐ » እንደተገለጸው ጠለፋውን የሚያስፈጽሙ መሳሪያዎችን ማስቀመጥ ወይም ማንሳት ይችላል።

ተቋዋሚ ፓርቲዎችን ለማንገላታት እና ለማሰር እንደሚውል በሰፊው ለሚጠበቀው ይህ ረቅቅ ህግ አንድን ተጠርጣሪ ለአራት ወር ያክል ፍርድ ቤት ሳያቀርብ ፓሊስ እንዲመረምር መፈቀዱን በንኡስ አንቀጽ 20 በእስር ስለማቆየት በሚለው ክፍል መገለጹን የዘጋቢያችን ሪፓርት ያስረዳል።እስካሁን በግልጽ ዜጎችን ለማንገላታት የተጻፈ ህግ ሳይኖር ወያኔ የፈለገውን እያሰረ እና እየገደለ እዚህ ደርሷል ያሉት ታዛቢዎች ዛሬ ደግሞ በሽብርተኛ ስም የዜጎችን የመገናኛ መሳሪያዎችን መጥለፍ እና መሰለል፤ቤታቸው ውስጥ ዘው ብሎ ገብቶ የመበርበር ፈቃድ ለደህንነት ክፍሉ ከተሰጠ በፓለቲካ ባላንጣዎች ላይ ገመድ ለማጥበቅ ወያኔ ቆርጦ መነሳቱን ያሳያል ብለዋል።

እስካሁን በግልጽ ዜጎችን ለማንገላታት የተጻፈ ህግ ሳይኖር ወያኔ የፈለገውን እያሰረ እና እየገደለ እዚህ ደርሷል ያሉት ታዛቢዎች ዛሬ ደግሞ በሽብርተኛ ስም የዜጎችን የመገናኛ መሳሪያዎችን መጥለፍ እና መሰለል፤ቤታቸው ውስጥ ዘው ብሎ ገብቶ የመበርበር ፈቃድ ለደህንነት ክፍሉ ከተሰጠ በፓለቲካ ባላንጣዎች ላይ ገመድ ለማጥበቅ ወያኔ ቆርጦ መነሳቱን ያሳያል ብለዋል።

**(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## ትብብር ለምን?

የመተባበርን አስፈላጊነትና ጠቀሜታን ማንም አይስተውም:: «ለአንድ ብርቱ ሁለት መድሃኒቱ»፣ «ድር ቢያብር አንበሳ ያስር»፣ «ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ብርቁ ለሃምሳ ሰው ጌጡ ነው» እነዚህንና ሌችም ምሳሌዎች የመተባበርን ጠቀሜታነት ማህበረሰባችን በቅጡ የተረዳ ለመሆኑ ማስረጃዎች ናቸው::

የመተባበርን ጠቀሜታ ለመረዳት ፖለቲካ ውስጥ መግባት አያስፈልገም::የመለስ ዜናዊ አይነቱ በመንደር ዱርዬ መርህ የሚመራ እብሪተኛ የፖለቲካ ባላንጣ እንዲገጥመን የሚጠይቅ አይደለም:: እንኳን አዋቂዎች ህጻናትም ሳይቀሩ በተናጠል ከሚሰሩት፣ ተባብረው የሚሰሩት ውጤት የማምጣት እድሉ የላቀ እንደሆነ ያውቃሉ::

በማህበራዊ ህይወታችን ውስጥ በተናጠል ከምንሰራቸው ስራዎች ይበልጥ መተባበርንና መደጋገፍን የሚጠይቁት ብዙዎች እንደሆኑ እናወቃለን፤፤ ከእነዚህ ጉዳዮች መሃል ፖለቲካ አንዱ ነው:: ፖለቲካ ማህበራዊ እንቅስቃሴ እንደመሆኑ መጠን በጋራ የተሰባሰቡ ዜጎችን ጥረት የሚጠይቅ ነው:: የግል ፖለቲካ ብሎ ነገር የለም:: ለዚህ ነው ዜጎች ተደራጅተው ፖለቲካ የሚያካሂዱት:: በተለይ ደግሞ ፖለቲካው መለስን የመሰለ ጉልበተኛ የገነነበት ሆኖ ሲገኝ ደግሞ፣ ይህን ጉልበተኛ ለመስታገስ የበለጠ ትብብር እንደሚያስፈለግ ገልጽ ነው:: ስለእዚህ ዛሬ የሃገራችን ፖለቲካ ያለበትን ችግር ለመቅረፍ፣ በአምባገነንነት ምትክ ሁሉንም ዜጎች በእኩልነት የሚያስተናግድ የፖለቲካ ስርአት ለመገንባት የመለስ ዜናዊን እብሪት አምረው የሚጠሉ ተባብረው የመስራታቸው አስፈላጊነት የማያጠያይቅ ነው:: ስለእዚህም ነው ግንቦት 7 የመተባበርን አስፈላጊነት ለማስረዳት የምናጠፋውን ግዜ፣ ትበብር ለምንና እንዴት የሚሉትን ጥያቄዎች ለማንሳትና ምልሻቸውን ለመስጠት ልናጠፋው ይገባል የሚለው:: ትኩረታችንን ሊስብ የሚገባው፣ ትብብሮች እንዴት ሊፈጠሩ ይችላሉ? ከተፈጠሩም በኋላ ተጠናክረው እንዴት ይቀጥሉ? የትብብሮች መነሻና መድረሻ ምን ይሁን? የሚሉት ጥያቄዎች ሊሆኑ ይገባል::

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ የመለስ ዜናዊን አምባገነንነት መጥላት ብቻ በቂ አይደለም:: መለስ ዜናዊ በፈጠረው አምባገነናዊ ስርአት ምትክ ምን እንተካ የሚል ጥያቄ ማንሳት፣ ይህንን ስርአት በምን ሂደት አልፈን እናምጣው፣ የተለያ የፖለቲካ ድርጅቶች የስራ ሃላፊነት ምን ይሆናል የሚሉትን አስቸጋሪ ጥያቄዎች መመለስ ይጠይቃል::

ለእዚህም ነው ግንቦት 7 ገና እንደ ንቅናቄ ሲጸነስ የመተባበርን አስፈላጊነት መስበክ ብቻ ሳይሆን፣ ትብብር ከማን፣ ለምንና አንዴት የሚሉትን ጥየቄዎች በማንሳት የማያሻማ ምላሽ የሰጠው::

ለመተባበርና ተባብረንም ለመዝለቅ አብዛኞዎቹ የፖለቲካ ድርጅቶችና አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ሊደግፏቸው የሚችሉ ከውዝግብ ነጻ ከሆኑ መሰረታዊ የመተባበሪያ ነጥቦች ያስፈልጋሉ ከሚል እምነት በመነሳት ግንቦት ሰባት የሚቀጥሉትን ቁም ነገሮች አስቀምቷል::

1. መለስ ዜናዊ ሳይገደድ ወይም ሳይወገድ በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ስርአት መገንባት አይቻልም
2. የመለስ ዜናዊንና ጥቂት ግብረ በላዎቹን ለማስገደድ ወይም ለማስወገድ የሚሰባሰቡ ሃይሎች በሃገራችን በሰፈነው አምባገነናዊ ስርአት ምትክ የሚተኩትና ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአት የሚገነባበት ኢትዮጵያ የምንላት አንዲት ምሉእና ልኡዋላዊ ሃገር መሆኗን መግባባት ይኖርባቸዋል

ይህ ትብብር መለስን አስገድዶ ወይም አስወግዶ በዘረኛ አምባገንንን የፖለቲካ ስርአት ምትክ ስለሚተካው የፖለቲካ ስርአት የጋር ስምምነት ሊኖረው ይገባል:: ይህም የፖለቲካ ስርአት የጥቂት ምርጦች መንግስት ሳይሆን፣ ህዝብ በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ የሰየመው መንግስታዊ አስተዳደር ይሆናል::
ከእዚህ በላይ የቀረቡት ሶስት ነጥቦች ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ለመተባበር በቅድሚያ ሊስማሙባቸው የሚገቧቸው ነጥቦች ናቸው:: ግንቦት 7 እነዚህ ብቻቸውን ለመተባበር በቂ ናቸው የሚል እምነት የለውም::

መተባበሩ እንዲዘለቅና የሚተባበሩት ሃይሎችም በመለስ ዜናዊ አምባገነናዊ አገዛዝ እግር ለመተካት የሚመኙት በምርጫ የሚመጣው ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ህልም እንዲሰምር፣ ይህ እንዴት እውን ሊሆን ይችላል የሚል ጥያቄ በመንሳት በምላሹ ዙሪያ አስቀድመው መስማማት አለባቸው::

ግንቦት 7 በእዚህም ነጥብ ዙሪያ ግልጽ አቋም ወስዷል:: የግንቦት 7 አቋም በዋንኛነት የመነጨው የኢትዮጵያ ህዝብ በ1997 ምርጫ ያሳየውን የፖለቲካ ብስለት፣ ለመብቱ መከበር የከፈለወን መስዋእትነት፣ ይህ መስዋአትነት የታለመለት ግብ እንዳይመታ ካደረጉት ምክንያቶች የሚመነጭ ነው:: በመሆኑም የሚቀጥለው መንግስታዊ አስተዳደር በህዝብ ነጻና ፍትሃዊ የምርጫ ተሳትፎና ውሳኔ ሊመጣ የሚገባው መሆኑን የተግባቡ ሃይሎች ለመተባበር ከሚስማሙባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች አንዱና ቁልፉ ይህንን አይነቱን ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ በሃገራችን አንዴት እውን ማድረግ ይቻላል የሚለው ነው:: ግንቦት 7 ለእዚህ ጥያቄ የሰጠው መልስ ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ፣ ነፃ የፍትህ ስርአት፣ ከፖለቲካ ያልወገነ የመከላከያ የደህንነትና የፖሊስ ሃይል፣ ነጻ መገናኛ ብዙሃን፤ ከየትኛውም ምርጫ በፊት በሃገራችን ሊኖሩ ይገባል የሚለውን ነው:: በእዚህ ላይ ስምምነት ሳይያዝ የሚፈጠር እውነተኛ ትበብር ሊኖር አይችልም:: ትብብር ቢኖርም ህዝብን ያላሳተፈ የምርጦች ትብብር ብቻ ነው መሆን የሚችለው:ህዝብን የሚጠቅም ዘለቄታነት ያለው ትበበር ከቶውኑ ሊሆን እንደማይችል ግንቦት 7 ጽኑ እምነት አለው::

በመጨረሻም፣ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት የመተባበሪያ ምእራፎች ላይ መግባባት ከተደረሰ በኋላም ይህን ስምምነት እንዴት በጋራ በተግባር እናውለዋለን በሚለው ጉዳይ ላይ ተጨማሪ የጋራ ግዛቤ ሳይኖር ትብብሩ የትም ሊደርስ እንደማይችል ግንቦት 7 ያምናል:: መለስን አስገድደው ውይም አስወግደው ነጻ ተቋማት በመገንባት፣ በህዝብ ምርጫ የሚሰየም መንግስታዊ አስተዳደር ለመመስረት የተስማሙ ሃይሎች፣ ይህንን አንዴት ተግባራዊ ለማድረግ አንደሚችሉ አስቀድመው ጥያቄ ማንሳት ይኖርባቸዋል:: እዚህ ላይ ለማንሳት የተፈለገው የሚተባበሩትን ሃይሎች የትግል ስልት አይደለም:: አምባገነናዊውን ስርእት አስወግዶ ህዝብ በምርጫው በሚሰይመው ስርአት መመስረት መሀል የሚፈጠረውን የስልጣን ክፍተት እንዴትና በምን እንሙላው የሚለውን ጥያቄ ለማንሳት ብቻ ነው::

ግንቦት 7 ለእዚህም ጥያቄ የማያሻማ መልስ ሰጥቷል:: በኢትዮጵያ ውስጥ መቋቋም ስለሚገባው፣ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ስለሚሰየም መንግስት ስምምነት የደረሱ ሃይሎች፣ ይህንን ስምምነታቸውን ማስፈጸም የሚችሉባቸውን ነጻና ገለልተኛ መንግስታዊ ተቋማት ለመገንባት አንድ አይነት የጋራ የሽግግር መንግስት ማቆም እንደሚኖርባቸው ግንቦት 7 በግለጽ አስቀምጧል:: የእዚህ መንግስት ዋንኛ ተግባርም፣ ህዝብ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ በአስቸኳይ አድርጎ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በታሪካችን ለመጀመሪያ ግዜ የሚደረግ የስልጣን ርክክብ ለማድርግ እንደሆነ ግንቦት7 አስምሮበታል:: ይህ የሽግግር መንግስት ምን አይነት ቅርጽ ይኖረዋል ለሚለው ጥያቄ መልሱን የተባበሩት የፖለቲካ ድርጅቶች በሚጠሩት ታላቅ ሸንጎ የሚወሰን ይሆናል የሚል አቋም ግንቦት ወስዷል:: የተረጋጋ ሽግግር ለመፍጠር ግን ይህ ውይይት በሰለጠነና አምክህኖታዊ በሆነ መንገድ ከአሁኑ መጀመር ይኖርበታል::

በግንቦት 7 በኩል ስለመተባበር አስፈላጊነት ብቻ ሳይሆን ትብብር ለምንና እንዴት ለሚሉት ጥየቄዎች መልስ ሰጥተናል:: የሃገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች ስለትብብር አስፈላጊነት ሲያትቱ በተመሳሳይ ትብብር ለምንና እንዴት የሚለውን ጥያቄ አንስተው መልስ ቢሰጡ የሃገራችንን ችግር ለመፍታት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው:: ህዝብም በየግዜው የፖለቲካ ድርጆቶቹ ለሚያወሩት የመተባበር አስፈላጊነት ድጋፉን መስጠት የሚችለው ይህ ትብብር ለኔ ምን ይፈይዳል ለሚል ጥያቄው መለስ ካገኘ ብቻ ነው:: ከእዚህ ውጭ በመተባበር ስም የሚፈጠሩ ግንባሮች ቅንጅቶች፣ ምድረኮችና ህብረቶች ከእዚህ ቀደም ተፈጥረው ከነበሩ ፍጻሚያቸው ሳያመር ከከሰሙት ትብብሮች አሳዛኝና አሳፋሪ እጣ የተሻለ እድል ሊኖራቸው አይችልም:: ስለእዚህም ነው፣ ግንቦት 7 ስለመተባበር አስፈላጊነት ድምጻቸውን አጉልተው ለሚጮሁ ድርጅቶች፣ ቡድኖችና ግለሰቦች በሙሉ የመተባበሪያ አጀንዳቸውን ለህዝብ ግልጽ እንዲያደርጉና ህዝብም በእነዚህ በጋራ ሁላችንም በምንስማማባቸው ነጥቦች ዙሪያ ድጋፍ እንዲሰጠን በጋራ ጥሪ እናደርግ የሚለውን የራሱን ጥሪ በወገናዊ ስሜት የሚያቀርበው::

## ውድ አንባቢዎቻችን

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።**

g7radio@ginbot7.org



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ከወሬ ወደ ተግባር፤ ፋና ወጊው የግንቦት 7 ስብሳባ በፍራንክፈርት

አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ

## ፍርሻ

እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር የካቲት 28 2009 ዓ.ም. በእለተ ቅዳሜ፣ የግንቦት7 ንቅናቄ በጀርመኑ ከተማ በፍራንክፈርት ላይ ከኢትዮጵያውያን ጋር ለመወያየት ስብሰባ ጠርቶ ነበር:: በእዚህ ስብሰባ ላይ ግንቦት 7ን ወክዬ ማብራሪያ እንድሰጥ በንቅናቄው የተፈረደብኝ እኔው ነበርኩ:: ፍርሻ ያልኩት ስቀልድ አይደለም:: ከምሬ ነው:: ሰብሰባ፣ ክርክር፣ ሙግት፤ እንዲሁም ጥሩና መጥፎውንም፣የሰለጠነውንምና ያልሰለጠነውንም ጠያቂና ጥያቄ ማስተናገዱ ስለሚያስፈራኝ አልነበረም ፍርሻ ያልኩት:: ፍርሻ ያልኩት እኔን ለማዳመጥ የሚሰበሰቡት ወገኖቼ፣ አንዳንዶቹ ከተለያዩ የአውሮፓ ከተሞችና የጀርመን ከፍለ ሃገሮች ድረስ ረጅም ጉዞ ተጉዘው እንደሚመጡ አስቀድሜ ሰምቼ ነበር:: ቀሪዎቹም ስብሰባው እንዲሳካ እዛው ፍራንክፈርት ላይ እየደከሙ እንደነበር ስለማውቅ፣ የእነዚህን ወገኖቼን ድካም የሚመጥን ምን ይዤ ልቅረብ የሚል ጭንቀት ነው ተልዕኮየን እንደ ፍርሻ እንዳይ ያደረገኝ::

## የፍርሻው መፍትሄ

ይህንን ጉዳይ አቅልዬ ልወስደው አልፈለግሁም:: ፍርሻ እንዳይሆን ምን ማድረግ እንዳለብኝ ራሴን ጠየቅሁ:: መልሱ ቀላል ነበር:: ስብሰባው እንደተለመደው አንድ ሺህ ግዜ በአንድ ሺህ ስብሰባዎች አንስተን የጣልናቸውን ጉዳዮች መልሰን የምናመነዥክበት እንዳይሆን ማድረግ ብቻ መሆኑ ገባኝ:: እርግጠኛ ነኝ በሃገሩ ጉዳይ ሆዱ አልቆርጥለት ብሎ የሚሰበሰበው አብዛኛውን ወገኔንም የሚፈልገው ይኸንኑ ነው ብዬ ገመትኩ:: ስብሰባዎች ከወሬ ያለፈ የረባ ነገር ጠብ የሚልባቸው አለመሆናቸው፣ ሁላችንም እንደፍርሻ እድናያቸው ሆኗል:: ስብሰባዎቻችንን አስጨናቂ የሚያደርጋቸው፣ ተግባርን ግባቸው ያደረጉ ወይይቶች የምናደርግባቸው አለመሆናቸው እንደሆነ ከተረዳሁ ቆይቻለሁ:: ሆኖም ግን ለመፈትሄው ተጨንቄ መላ መትቼ አላውቅም::

ተሰብሳቢው ለትራንስፖርት ያወጣውን ገንዘብና ግዜ፣ በስብሰባ አዳራሽ ተቀምጦ የሆነ ያልሆነውን በመስማት የሚያጠፋውን ተጨማሪ ገንዝብና ግዜ አሰብኩት:: የስብሰባ አዘጋጆቹ ያበሰሉትን በመቅመስ፣ ያቀረቡትን በመጠጣት የሚጠፋውን ሌላ ተጨማሪ ገንዘብ ገመትኩት:: የገንዘብ ጉዳይ ሲነሳ ደግሞ ክሬዲት ክረንች የሚሏትም የምእራብ ኢኮኖሚን እያመሰች ያለችው በሽታም ታወሰችን :: ከሁሉም በላይ ማለቂያ በሌለው ጉጉቱ፣ በተስፋ ስሜቱ ተሰብሳቢው የሚከፍለውን በገንዝብ ሊገመት የማይችል ወጪ ሳስበው ስብሰባን ወጤት የሌለው የጉንጫ ማልፋት ጨዋታ አደርጎ መውሰድ ወንጀል ሆኖ ተሰማኝ:: እኔም ብሆን ተመሳሳይ ወጪ አለብኝ:: ተሰብሳቢው ብቻ አይደለም ለኪሳራ አደጋ የተጋለጠው:: ተሰብሳቢና ሰብሳቢ ሁሉም ይህንን ሁሉ ወጪ አድርገው የሚጠራ ስብሰባ ፍሬ ከርስኪ ተነግሮባቸው፣ ተሰብሳቢውም ተሰላችቶ እያዛጋ እኔም በሚያንገሸግሽ ስሜት አንድ ፈታኝ ቀን እዳለፈ ለራሴ እየተናገርኩ መመለስ የለብኝም አልኩ:: ወዲያው ወሰንኩ:: ይህ ስሜት በስብሰባው የሚገኘው የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ስሜት እንደሆነ ለማወቅ ጠንቋይ መቀለብ አልነበረብኝ:: መልሱ ቀላል ነበር:: እነ አጅሬ እንደሚሉት የሮኬት ሳይንቲስት መሆንን የማይጠይቅ:: አይን ከፍቶ ማየት ብቻ ነው የሚያስፈልገው::

## በጎ ቅናት ለፈረንጆቹ፤ ሌቱ እንዲነጋ

የፍራንክፈርት ስብሰባ የተጠራው ጀርመንን ቀፍድዶ ይዞት የነበረው ደመናና ቆፈን ተነስቶ፣ ቀኑ ጸሃያማ አየሩም ሞቅ ማለት በጀመረበት እለት ነው:: ቅዳሜ ቀን ነውና ሲሰራ የሰነበተው ሁሉ የማረፊያው እለት ነው :: የአየሩ መለወጥ የጀርመኑን ዜጋ ፈገግ እንዳስደረገው በየመንገዱ የሚታየው የነጭ ፊት ሁሉ ይመሰክራል:: የእኛም ሰዎች “እግርህ መልካም ነው መልካም አየር ይዘህ መጣህ” ብለውኛል:: እንግድነቴን በማክበር:: ጸደይ የመጣ መስሏችው እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሄዱ ፍቅረኞች አይቻላሁ:: ጣትና ጣታቸውን አቆላልፈው ከሚነጉዱት ወጣት ፍቅረኞች እድሜ በላይ በአውሮፓ ኖሪያለሁና፣ የአውሮፓ ክረምት ወጣ ሲሉት እንደሚመለስ አውቃለሁና እነዚያ ጣቶች መልሰው ጓንት ውስጥ እንደሚገቡ ጠርጥሪያለሁ:: ህጻናት ልጆቻቸውን ወደ መናፈሻ ቦታ የሚጎትቱ ወላጆችም ተመልክቻለሁ:: የፈረደባቸውን የኔዎቹንም በእንግሊዝ ምድር ለፈረደባት እናታቸው የተውኳቸው ትንንሾቹ ውልብ ብለውብኝ አለፉ:: የቡድናቸውን ማልያ ለብሰው የእግር ኳሱ ጨዋታ እስኪጀመር በረጃጅሙ የጀርመን ብርጭቆ ቢራቸውን የሚገለብጡ ደጋፊዎች በየቢራው ቤት በራፍ ላይ ተደርድረዋል:: ፍረንክፈርት፣ ሻካን የተባለውን ቡድን በእለቱ እንደሚገጥም መንገድ ላይ ከተለጠፈው ማስታወቂያ ተረድቻለሁ:: ኳስና እኔ ብቻ ምን ይደረግ! ነበር መልሴ ቢራ እየገለበጡ በደስታ ለሚያወጉት ባለማሊያዎች:: በግዜ የቤት ስራውን የሰራ ህዝብ ቀልቡን ጥሎ ይደሰታል፤ ወይ መታደል! እያልኩ ነበር ወደ ስብሰባው አዳራሽ የገባሁት:: ይህንን አይነት ስሜት ሲያድርብኝ የመጀመሪያው አልነበረም::

በተለይ ፈረንጁ በደስታ በሚፈነድቅባቸው የበጋ ወራት እኛ ኢትዮጵያውያን አዳራሽ ሞልተን፣ የአየር ማቀዝቀዣውን ጉልበት ሰብሮ በሚመጣ ወበቅ በላብ እየሾቅን ስለረሃብና ስለሞት ስለታሰሩትና ስለተሰደዱት በምሬት ስንናገር ባየሁባቸው ስብሰባዎች በሙሉ በእኛ ዘግኛኝ እጣ ያላዘንኩበት ቀን የለም:: ታላቁን ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድህንን ከብዙ ዘመን በኋላ ጠይቄው እራሱ እንኳን ማስታወስ ያልቻለውን ስንኝ፣ በተለይ በበጋ ወር የበጋ ወር በአሜሪካና በአውሮፓ የምናደርጋቸው ስብሰባዎች ሁሌም እንዳስታወሱኝ ነው::በወጣትነት እድሜዬ ባለቅኔው የተኛበትን የስሚንቶ ወለል በእኩልነት ለመካፈል በታደልኩበት አጭር የእስር ዘመን ነበር፣ ጸጋዬ የእስር ቤቱን ጥበት፣ የእስረኛውን ብዛት፣ በገዛ ላቡ መሾቁን፣ በእስትንፋሱ መንፈሩን፣ ከእስረኛው ትንፋሽ ወደጣራው እያረገ ተመልሶ የሚንጠባጠበውን ወሃ እየተመለከተ

«እዩት የሰው አሹቅ የሰው ንፍሮ
ሰው በሰው ላይ ተደራርቦ
ሰው በሰው ተነባብሮ»

በማለት ቅኔውን የዘረፈው:: ከትቦትም በወረቀት አይቻለሁ፤ የእቴጌና የጃንሆይ ምስል በተቀረጸባት ባለ አስራ ስድስት ገጽ የተማሪ ደብተር:: ይህ ኩነት ከተከናወነ ከሰላሳ አመት በኋላ ጸጋዬ የለም:: እኔም ሆንኩ በየግዜው በየስብሰባው የማገኛቸውም ኢትዮጵያውያን ነጻነት በሰፈነባቸው የምእራባውያን መዲናዎች ውስጥ ነው የምንኖረው። ህይወታችን ግን፣ የበጋ ወር ስብሰባዎቻችን ግን፣ የጸጋዬን ግጥም ደግመው ደጋግመው እንዳስታወሱኝ ነው:: አለም ለእኛ ለአበሾች ሰፊ እስር ቤት እንደሆነ ነው የሚነግሩኝ:: በማሪየት ሆቴል የመሰብሰቢያ አዳራሽና በ69 ዓ.ም. ባለቅኔው ጸጋዬ ከሁለት መቶ በላይ ወገኖቹ ጋር በታሰረበት የአንደኛ ፖሊስ ጣቢያ ትንሽ ክፍል መሃል ልዩነቱ ምንድነው?

መቼ ነው ይህ ሰቆቃ የሚያበቃው? የተለመደ፣ ከጸጸት የሚወለድ፣ በየስብሰባው መሃል በዝምታ የማነሳው ጥያቄ ነው::

## ጥያቄና መልስ፣ ከራስ ጋር ፍጥጫ

ይህንን እውነታ የሚከድ ኢትዮጵያዊ የሚኖር ስላልመሰለኝ ለፍራንክፈርት ታዳሚዎች አንድ ነገር ለማቅረብ ወሰንኩ:: «መሰብሰባችን ካልቀረ ስብሰባውን ሌላው ቢቀር እርባና ግብ ያለው እናድርገው» ለማለት ተዘጋጀሁ:: ጮርቃ አይደለሁምና ጉዳዩ ዝም ብሎ «ስብሰባችንን እርባና ያለው እናድርገው» በማለት ግን የትም እንደማይደርስ ለማወቅ አልተቸገርኩም:: በብዙ ስብሰባዎች መጀመሪያ ስብሰባውን በሚመለከት የሚሠጡ ቀና ማሳሰቢያዎች ተጥሰው፣ ስብሳቢውና ተሳታፊው በጥቂት ይሉኝታና ደንታ በሌላቸው ግለሰቦች ታግተው፣ እስከሚያንገሸግሻቸው ድረስ የዛገ የሻገተ ወሬዎች ሲጋቱ አይቻለሁ:: በመሆኑም ከማሳሰቢያ በላይ ያለፈ ሌላ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ አውቂያለሁ:: መፍትሄ አድርጌ የወሰድኩት ከሁሉም ነገር በፊት ይህንኑ ጉዳይ በቅድሚያ ለታዳሚው ባቀርብለትና እራሱ ቢወስንበት ብዬ አሰቢያለሁ::

ለእኔ እድል ተሰጥቶኝ መናገር ከመጀመሬ በፊት ስብሰባውን እንድትመራ በሊቀመንበርነት የተመደበችው እህቴ እኔን አስተዋወቀች፤ ስብሰባው እርባና ያለው እንዲሆን መከረች:: አስቀድማ ግን እኔ ያሰብኩበት ጉዳይ ምን እንደሆነ ስላልነገርኳት የመሰላትንም እንደመሰላት ጨመረችበት:: መልካም ጅማሮ ነበር:: በመጨረሻም መድረኩን ለአቶ አንዳርጋቸው አስረክባለሁ አለች:: ክቡር የሚለውን ቃል ከስሜ ፊት አስቀድማ::

ይሁን ብዬ ተቀበልኩና፣ ወገኖቼ «ንግግሬን ከመጀመሬ በፊት ከእናንተ ጋር ስብሰባውን በሚመለከት ውል መግባት አለብኝ» አልኳቸው:: ሳስበውና ሳሰላስለው የነበረውን የእኛን የኢትዮጵያውያንን ጎጂ የስብሰባ ባህል ዘረገፍኩ:: ከልብ አድማጭ ማግኘቴን ሰለተረዳሁ፣ የስነጽሁፎቻችንንም ድክመት ለመግለጽ ሞከርኩ:: ድህረ ገጾቻችንን፣ ፓልቶክ ክፍሎቻችንን እና የምንሰጣቸውን ቃለ ምልልሶች ድክመቶች አዥጎደጎድኩ:: ያቀረብኩት ሂስ ጥቅል በመሆኑ የምለውን ለማጠናከር በምሳሌ ደገፍኩት:: «አንዱ ችግራችን መፍትሄን ማእከል ያደረገ የአስተሳሰብ ምህዳር የለንም:: ችግርን ብቻ በሚዘረዝር አዙሪት ውስጥ ወድቀናል:: ችግርን መዘርዘሩን ግብ አድርገነዋል:: እራሱ ውጤት ሆኖ መታየት ጀምሯል:: ብዙ ድካምና ወጪ አድርገን ስብሰባ መጥተን ምንም የረባ ነገር ሳንሰራ እንበተናለን:: ይህ አሰመርሮ ግን ከስብሰባ አያስቀረንም:: አደንዛዥ እጽ እንደለመደ ሰለባ እኛም የእዚህ አይነቱ ራስን የሚተለትል የስብሳባ ባህል ሱሰኞች ሆነናል ወይ?» ብዬ ጠየቅሁ:: «ታዲያ እንዴት ነው ይህንን የመከነ የስብሰባ፣ የጽሁፍ፣ የውይይት ባህል ሳንሰብር በሃገራችንና በሁላችንም ላይ የተከመረውን መከራና መርገም ከራሳችን ላይ ማንሳት የምንችለው? ለመሆኑ የወያኔ ግፍ በውግዘት ጋጋታ ያከትማል? ችግር፣ ችግር መሆኑ ስለተነቃበት ብቻ አገር ጥሎ ይጠፋል? አይመስለኝም» አልኩ። «ተነጋግረን ችግራችንን ከተረዳዳን፣ የሚቀጥለው እርምጃ መፍትሄ መፈለግ ነው:: መፍትሄው ላይ ስምምነት ከተደረሰ ደግሞ የሚቀጥለው እርምጃ የጋራ መፍትሄን በጋራ ይዞ ወደ ተግባር መጓዝ ነው:: እነዚህ ሶስት እርምጃዎች ከተነጣጠሉ ግን፣ ፈረንጅ የቤት ስራውን ጨርሶ ሲደሰት እኛ የዘላለም የልቅሶ እርግማናችንን ተቀብለን መቅረታችን ነው» አልኩ:: አከታተልኩና «በእዚህ ልዩነት ስለማይኖር ወደ መፍትሄው ብሄድ» ብዬ ሳማክር ሁሉም የሚያቃጥለውና የሚያበግነው ጉዳይ ነውና በአንድ ድምጽ «ቀጥል» ተባልኩ::

«ለእዚህ ስብሰባ ርእስ ይሰጠው ቢባል፣ የምሰጠው ርእስ 'ከወሬ ወደ ተግባር' የሚል ይሆናል» ብዬ ጀመርኩ:: «ስብሰባችን ሲያልቅ በተጨባጭ የተገኘ ውጤት ከሌለ እናንተም ከስራችኋል ግንቦት 7ም ከስሯል ብዬ አምናለሁ:: ይህ ስብሰባ የተጠራው ግንቦት 7ን ለማስተዋወቅ፣ በንቅናቄው ፕሮግራም፣ በሚከተለው የትግልና የፖለቲካ ታክቲክና ስትራተጂ ጉዳዮች ላይ ገለጻ ለማድረግ ነው:: ከእዚህ ገለጻ በኋላ አብዛኞቻችሁን በማሳመን የግንቦት 7 እቅድ እንዲሳካ በገንዘባችሁ፣ በእውቀታችሁ፣ በግዜያችሁና በጉልበታችሁ ተጨባጭ ድጋፍ ለማድረግ የሚቻልበትን ሁኔታ ለመፍጠር ነው:: እናንተም የተሰበሰባችሁት የግንቦት 7 ስብሰባ መሆኑን አውቃችሁ ነው:: ግንቦት 7ን በውል እንወቀው ብላችሁ፣ ካወቃችሁትም በኋላ ካመናችሁበት ልትቀላቀሉት፣ ልትደግፉትና ልታበረታቱት እንጂ ሌላ ነገር በእዚህ ስብሳበ ይገኛል ብላችሁ እንዳልመጣችሁ እርግጠኛ ነኝ:: እናንተም ይህ ፍላጎታችሁ ሳይሳካ ቢቀር አይ ግዜዬ! አይ ገንዘቤ! አይ ኢትዮጵያ እያላችሁ! በጸጸትና በምጸት ታጅባችሁ ወደመጣችሁበት አንገታችሁን ደፍታችሁ ልትመለሱ ነው:: ይህን ደግሞ እንደማትፈልጉ ይገባኛል» አልኩ:: ሁሉም የተስማማ ስለመሰለኝ «እንግዲህ ይህንን ለማሳካት በቅድሚያ ለምናደርገው ውይይት ትርጉም የሌላቸውን ብዙውን የኢትዮጵያውያንን ስብሰባ ከወሬ እንዳያልፍ ቀይደው የያዙትን ነጥቦች በእዚህ ስብሳባ እንዳይነሱ እንገድብ:: በቅድሚያ በተስማማንበት አጀንዳ ላይ ያተኮረ ስብሰባ እንድናደርገው እንስማማ» አልኩኝ:: ይሁንታ ስላገኘሁ በእዚህ ስብሳባ ሊነሱ አይገባቸውም ብዬ ያሰባሰብኳቸውን ጉዳዮች ደረደርኩ:: በጥያቄ ነበር የጀመርኩት::

«ስለወያኔ ክፋትና ጥፋት፣ በሃገርና በወገን ላይ ስለፈጸመው ወንጀል እዚህ የማያውቅ አለ ወይ?» አልኩ፡፡

«የለም» የሚል መልስ ሳገኝ፣ «እኔም ሆነ እናንተ ውድ ግዚያችንን ስለወያኔ መጥፎነት ተራ በተራ እየተነሳን በመናገር ውድ ግዚያችንን ማጥፋት አለብን ወይ?» ብዬ ጠየቅሁ፡፡ የተሰብሳቢው መለስ ግልጽ ነበር፡፡ ሌሎችንም ነጥቦች አነሳሁ፤ ስለቅንጅት መከፋፈል ብዙ መግለጫዎች፣ ስብሰባዎች እና ቃለ ምልልሶች ተሰጥተዋል፡፡ ሽህ ግዜ የተነሳ ጉዳይ ነው፤ ዛሬም እዛው ውስጥ ተመለስን እናቡካ ወይስ ይብቃን?» ይብቃን ተወሰነ፡፡ «ግለሰቦችንና ደርጅቶችን ማውገዝ ወይም ማወደስ የኢትዮጵያን ችግር ያቃልላል ወይ? ህጻን ልጅ እንኳን የማይስተውን የመተባበር አስፈላጊነት፣ የመተባበር ጠቀሜታን አንድንናገር ሌላውም እንዲደግም ልንፈቅድ ይገባል ወይ?» አልኩ፡፡ «አይገባም» ተባለ፡፡ መተባበር ለምን ግብ፣ መተባበር አንዴት ለሚሉት ግን ግዜ መስጠት ተገቢ መሆኑን ተረዳዳን፡፡ ችግሩ ያለው እዚህ ላይ ነውና፡፡ ሌሎችንም ሰብሰባችንን ከወሬ ወደ ተግባር ለማሸጋገር እንቅፋት ይሆናሉ ያልናቸውን የብዙ ስብሰባ ውድቀት የሆኑ ጉዳዮች አስቀድመን ላናነሳ፣ እኔ ካነሳሁ ሊስያቆሙኝ እነሱ ካነሱ እኔና ሰብሳቢዋ እህቴ ተረዳድተን ልናስቆማቸው በቅድሚያ ተስማምተን ስብሰባው ተጀመረ፡፡

«ስለግንቦት 7 የምታውቁትን በዝርዝር በመድገም ግዜ አላጠፋም፡፡ በተለይ በውጭ የምትኖሩ ወገኖቼ በርካታ እድል ስላላችሁ ብዙውን በእጃችሁ ካለው በራሪ ሰነድ፣ ከድረገጻችን እንደምታገኙት አውቃለሁ፡፡ በራዴዮ፣ በፓል ቶክ እና በሌላም የመገናኛ ዘዴ በቂ መግለጫ ተስጥቶበታል፡፡ ይህንን መድገም ቀድመን በኮነንነው የወሬ ስብሰባ መጠመድ ስለሚሆን በአጭሩ በሶስት መሰረታዊ ነጥቦች ላይ የንቅናቄውን አቋም ገልጬ ቤቱን ለጥያቄና ለውይይት እከፍታለሁ» አልኩ፡፡

«የግንቦት ሰባት ፕሮግራም ምንድነው፣ ይህን ፕሮግራም ለማስፈጸም የሚጠቀምበት የፖለቲካ ስልት ምንድነው፣ ይህን የፖለቲካ ስልት በምን አይነት የትግል ሰልት ያጅበዋል» በሚሉ ሶስት ርእሶች ስር በአጭሩ አስቀመጥኩት፡፡ የተሰጠኝ 50 ደቂቃ ነበር፡፡ እኔ ግን በአስር ደቂቃ እጨርሳለሁ ብዬ በአስራ አምስት ደቂቃ አከናወንኩት፡፡ አስቀድሜ ከተሰብሳቢው ጋር በገባሁት ውል መሰረት በሰጠሁት አጭር ገለጻና ተሰብሳቢው በራሱ ከሚያቀው በመነሳት ጥያቄውን ማቅረብ ጀመረ፡፡ ጥያቄና አስተያየት እንለያለን ብለን አስቀድመን ስለተስማማንም ጥያቄዎች ድንቋ የስብሰባ መሪያችን በሰጠችው ምሳሌ መሰረት ‹ወተት ነጭ ነወይ?› በሚል መልኩ ቅልብጭ ብለው ቀረቡ፡፡ ለጥያቄዎችና ለመልሶች ከበቂ ግዜ በላይ ነበረን፡፡ ለአስተያየትም በቂ ግዜ ተረፈ፡፡ ምክንያቱም ወይይቱ አራባና ቆቦ አልረገጠም፡፡ መሰረታዊ የሆኑ ፈታኝ ጥያቄዎች የተነሱበት፣ ከእውነተኛ ጭንቀትና ተቆርቋሪነት የመነጩ ስጋቶች የተንጸባረቁበት ስብሰባ በደስታ አለቀ፡፡

## ***ማሳረጊያ***

«ከወሬ ወደ ተግባር» የሚል ርእስ የተሰጠው ስብሰባ በማያወላዳ መልኩ የግንቦት 7 ንቅናቄን ምንነት ታዳሚው በሚገባ እንዲረዳ ያደረገ ነበር፡፡ ተረድቶም የአቅሙን መዋጮ በማድረግ በገንዘብ ደገፈው፡፡ ከዛም አልፈው እንዴት እንርዳችሁ፣ እንዴትስ አባል ለመሆን እንችላለን የሚሉ ጥያቄዎች በርካታ ሰዎች እንዲያቀርቡ ያደረገ ስብሰባ ነበር፡፡ ከስብሰባው በፊት «ይህንን ስብሰባ የቤተ ሙከራ ስብሰባ ላደርገው ወስኛለሁ፡፡ ከተሳካ እኛም ሆንን ሌሎች ደርጅቶች ለሚጠሩት ስብሰባ ሞዴል መሆን ይችል ይሆናል ብዬ ለጥቂቶች ነግሬ ነበር፡፡ ሙከራው ሰርቷል፡፡ ኢትዮጵያውያን በወሬ የሚያጠፉት ግዜ የሌላቸው መሆኑን በፍራንክፈርቱ ስብሰባ አረጋግጠዋል፡፡ እስከዛሬም በከንቱ የባከነው ግዜ ይቆጫቸዋል፡፡ በእዚህ ስብሰባ የታየው የስብሰባ ባህል ለውጥ መጀመሩን የሚገልጽ ነው፡፡ ተሰብሳቢው በወሬ፣ በሃሜት፣ በውሸት፣ በውግዘት፣ በውዳሴ፣ ግዜዬን አታባክኑ፡፡ በምክንያት ላይ የተመሰረተ ሃሳባችሁን አቅርቡ፡፡ በእኔ የመዳኘት ችሎታ ተማመኑ፡፡ ሌላውን ሁሉ እርግፍ አድርጉት የሚል መልእክት አስተላልፏል፡፡

«ታዲያ ይህን ሁሉ ብዬ፣ ሁሉም ነገር ያለምንም ስቅታ ቀጥ ብሎ የሄደ ነበር» ብል ውሸታም ያደርገኛል፡፡ ፈረንጆቹ «አሮጌ ልምድ ለመሞት ጣር ይበዛበታል» እንዲሉ፤ ተሰብሳቢው አስቀድሞ አይነሱ ያላቸውን እርባና የሌላቸውን ጉዳዮች በማንሳት ግዜያችንን በትርኪ ምርኪ ነገሮች ለማጥፋት የሞከረ አልነበረም ማለት አይደለም፡፡ ይህን ለማድረግ የሞከረ አንድ ሰው ተገኝቷል፡፡ በየስብሳባው ለአመታት የማይደክማቸውና የሚሉት ነገር የሌላቸው ግለሰቦች፣ አንድ ሽህ ግዜ አንስተው የጣሉትን፣ ዝንተ አለም ሲቦካ ሲጋገር፣ እንደገና ሲቦካ የከረመን ጉዳይ ከውይይቱ እንብርት መሃል ሰንቅሮ ውይይቱ ሃዲዱን እንዲስት የሞከረ አንድ ሰው ተገኝቶ ነበር፡፡ አስቀድሞ ከህዝብ ውክልና ማግኘት የሚጠቅመው ለዚህ ነው፡፡ «እንዲህ አይነቱ ጉዳይ እንዳይነሳ ተሰብሳቢው አስቀድሞ ከወሰነባቸው ፍሬ ከርስኪ ጉዳዮች የሚመደብ ስለሆነ...» ብዬ መናገር ስጀምር ተሰብሳቢው ሳቀ፡፡

ውይይታችንም በዋነኛነት ያተኮረው በህዝብ የሚመረጥ መንግስት አምጥተን ፈሪሃ-ህዝብ የሚሰማው አስተዳደር በሃገራችን ካላቆምን “ምርጦች” ሁሌም በሃገርና ወገን ላይ የሚያደርሱት ወንጀል አይቆምም፡፡ እነዚህ “ምርጦች” ከሰማይ የተቀባሁ ነኝ የሚሉ ንጉስ ይሁኑ ወይም ምርጥ መኮንኖች የፈየደው አልነበረም፡፡ አሁንም ቢሆን አብዮታዊ ዴሞክራት ነን በሚሉ ዘረኛ “ምርጦች” ምትክ በሊበራል ዴሞክራሲ ስም በሚምሉ፣ የህዝብ ውክልና በሌላቸው “ምርጦች” ቢተኩ፣ የሃገርና ወገን ለቅሶ አያከትምም፡፡ እርስ በርሳቸው የሚመራረጡ “ምርጦች” ሳይሆኑ ህዝብ የመረጣቸውና በእዚህም የተነሳ የፖለቲካ ህልውናቸው መሰረት ህዝብ መሆኑን የሚቀበሉ፣ ህዝብ ፈሪሃ-ህዝብ የጫነባቸው ብቻ ናቸው ከስልጣን ብልግና፣ ከዘረፋና ከሀገር ክህደት ራሳቸውን የሚቆጥቡ፡፡ ይህ ነበር በስብሳበው የቀረበው መሰረታዊ የሃገራችን ችግሮች መፍቻ ቁልፍ ሀሳብ፡፡

ህዝብ መርጦ መሪዎቹን ይሰይም፡፡ በህዝብ የተሰየመ ህዝብን ይፈራል፡፡ ህዝብ መሪዎቹን ለመሰየም ብቃት አለው፡፡ ይህንን በ97 ምርጫ አረጋግጧል፡፡ የህዝብን ድካም መና ያስቀረው፣ የከፈለውን መስዋእትነት ያመከነው የህዝብን ፍላጎት የሚፈጽሙ ህግ ተርጓሚና አስፈጻሚ አካላት አለመኖር ነው፡፡ ለኢትዮጵያና ለህዝቧ የሚጨነቅ ህዝብን የስልጣን ባለቤት የሚያደርጉትን ነጻ ተቋማት ጥያቄ ከማንሳትና በሃገራችን በፍጥነት ህያው እንዲሆኑ ከመታገል ውጭ ሌላ የላቀ አጀንዳ ሊኖረው አይችልም፡፡ ይህንን አቋም ለመውሰድ ሀጋዊና ህገወጥ፣ ሰላማዊና አመጽ የሚሉ ከድርጅት ስም በፊትና በኋላ ሊለጠፉ የሚችሉ ታርጋዎች ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ ህዝብ የስልጣን ምንጭ ነው፡፡ ምንጭነቱን በድምጹ ለሚያረጋግጥበት ሁኔታ መፈጠር አቋም እንውሰድ የሚል ጥሪ ነው በግንቦት 7 የፍራንክፈርቱ ስብሰባ የተንጸባረቀው፡፡

በፍራንክፈርት ስብሳበ ላይም ተሰብሳቢው የስብሰባው የመጨረሻው ወሳኝ ሆኖ በመውጣቱ በየስብሰባው ይገጥመን የነበረው ችግር አበቃለት፡፡ ተሰብሳቢው የሰጠውን ውሳኔ ጥሶ ስብሰባውን ለማደፍረስ ሙከራ ያደረገው ምርጥና ልዩ ፍጥረት በተሰብሳቢው ሳቅ ብቻ ተደናግጦ ሹልክ ብሎ የወጣበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ ጥቂቶች በአብዛኛው ህዝብ ግዜ፣ ሃብትና እውቀት እንዳያላግጡ የፈሪሃ-ህዝብ በሃገር ፖለቲካ መስፈን ወሳኝ ነው ያልነው በትንሿ አዳራሽ ውስጥ ተረጋገጠ፡፡

እንደተለመደው እኔም ደረቅ ፖለቲካን ትቼ የዛሬውን ጽሁፌን ለየት አድርጌ እንድጽፍ ያደረገኝ በፍራንክፈርት ስብሳባ የታየው ፋና ወጊ መስሎ ስለታየኝ ነው፡፡ አይታወቅም! የኛ ትውልድ የራሱን የቤት ስራ በመስራት፣ መጪው ትውልድ፣ በስደት ኑሮአችን እንደምንቀናባቸው ፈረንጆች ቀልቡን ጥሎ በሃገሩ የሚደሰትበት፣ ያለፍራቻ ያሻውን ተናግሮ የሚውልበት፣ ስለማታ እራቱ የማይጨነቅበት ሁኔታ በሃገራችን መጥቶ ለማየት እድሉን እናገኝ ይሆናል፡፡ የተጠራጠርኩት እድሉ መምጣቱ ላይ አይደለም፡፡ እርሱ የማይቀር ነው፡፡ የኛ፣ በተለይ የኔ ትውልድ፣ ይህንን ለመየት ይታደል ይሆን? ይህ ብቻ ነው ጥርጣሪዬ፡፡

## በጸረ ሽብርተኝነት ስም.... (ከገጽ 1 የዞረ)

በፓለቲካ አስተሳሰቡ የሚለይን ቡድን ወይም ግለሰብን ጸረ ሰላም እና ጸረ ህዝብ ማለት የለመደው ወያኔ አሁን ደግሞ ሽብርተኛ የሚል መዝሙር እንደሚዘምር ይጠበቃል ያሉት ታዛቢዎች በተለይ በዚህን ሰዓት ህጉን ማውጣት የተፈለገው በሰላማዊ ትግል ተስፋ ቆርጦ ወያኔን ሊገባው በሚችል ቋንቋ በማናገር መብትና ነጻነታቸውን ለማስከበር ቆረጠው የተነሱ የህብረተሰብ ክፍሎች እየበረከቱ በመምጣታቸው ትግሉን የሚያስተባብሩትን ፓርቲዎች አጋዥ ናቸው በሚላቸው አንዳንድ የምዕራቢያዊያን አገሮች ፊት በሽብርተኛነት ለማስፈረጅ ባለው ቀቢጸ ተስፋ እንደሆነ መገመት አያስቸግርም ብለዋል ። በቡሽ አስተዳደር የተሳሳተ የውጭ ፖሊሲ ዘመን የጸረ ሽብርተኝነት ዘመቻ አጋሪነትን ለዲሞክራሲ ድፍጠጣ እኩይ ተግባር የተጠቀመው መለስ ዜናዊ ፡ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የፀጥታና የመከላኪያ ሃይሎችን በቀጥታ ዕዝ ሰንሰለት ውስጥ በማስገባት አጋዚ በተባለ ጨካኝ ጦር በርካታ ንጽሃን ዜጎችን በጠራራ ፀሃይ በአዲስ አበባ መንገዶች ላይ እንዳስጨፈጨፈ ይህም የህግ የበላይነት ባለበት አገር በሽብርተኝነት የሚያስወነጅል ክፍተኛ ወንጀል ምናልባትም ሳዳም ሁሴን በኢራቃዊያን ኩርዶች ላይ ከፈጸመው ወንጀል የሚስተካከል እንደሆነ ህዝባችን አይስተውም ። የአለም ታላላቅ የዜና አውታሮች የዘገቡት ያ ህጻንና አሮጊት ጭምር የተጨፈጨፉበት የሰኔ 1997 እና ጥቅምት 1998 መንግስታዊ ሽብር ፡ ቀደም ብሎ በጋምቤላ ፡ በኦሮሚያ ፡ በአማራ ክልልና በደቡብ ከደረስው ተመሳሳይ እልቂት ጋር ተዳምሮ በአጋዴን ንጽሃን ወገኖቻችን ላይ እስከዛሬዋ ቀን ድረስ እየተፈጸመ ያለው ፋሽስታዊ ሰቆቃ ፍትህ ሳያገኝ ፤ የወያኔ መሪዎች ለማርቀቅና ለማጸደቅ የሚጣደፉት የህግ ድንጋጌዎች በቆራጥ ኢትዮጵያዊያን መስዋዕትነት የሃይል ሚዛኑ ሲለወጥ የቆሻሻ ቅርጫት ማጣበቢያ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለንም ይላሉ አስተያየታቸውን የሰጡን አንድ የግንቦት 7 ንቅናቄ አመራር አባል ።

## በኢትዮጵያ ቴሌኮሚንከሽን ....... (ከገጽ 1 የዞረ)

የኢትዮድያ ቴሌኮሚኒኬሽንን ለቻይና አሳልፎ የሰጠው ወያኔ በዋነኛነት ታሳቢ ያደረገው የመረጃ ፍሰትን መግታት እንደሆነ ታውቋል።ማንኛውም ኢትዮድያዊ እንደሚያውቀው በርካታ ድረገጾች እና ብሎጎች በቻይናውያን እርዳታ መታገዳቸው ነው። ባልታወቀ ምክንያት በዚህን ሳምንት መጀመሪያ ላይ አንዳንድ ድህረ ገጾች ተለቀው የነበረ ቢሆንም ከትናንት ጀምሮ ግን ችግሩ መልሶ መከሰት መጀመሩን ምንጮቻችን አስታውቀውናል ። ይሁን እንጂ ወያኔ ድረገጾቹን እና ብሎጎቹን ለማገድ በቻይናዎያን ላይ ጥገኛ የሆነው ኢትዮድያ ቴክኒሻኖች ስራውን ስለማይችሉት ሳይሆን ስለማይታመኑ ነው ብለዋል።ወያኔ ሳር ቅጠሉን ሁሉ ተጠራጥሮ እስከመቼ እንደሚዘልቀው የጠየቁት የውስጥ አዋቂ ምንጮች በራሱ ፍርሀት እና ጥርጣሬ ሀገሪቱን እንዳለ ለውጪ ዜጎች ቸርችሮ እንዳይጨርስ ፍርሀት አለን ብለዋል።

የኢትዮድያ ቴሌኮኒኬሽን ባለሙያዎች በገዛ ሀገራቸው አንገታቸውን ደፍተው ቻይናዊያኑን እየፈሩ የሚኖሩበት ሁኔታ እንደተፈጠር የተገለጸ ሲሆን ቻይናዊያኑ <<ከስራችሁ ልናባርራችሁ እንደምንችል ታዉቃላችሁ?እርፋችሁ ብትቀመጡ ይሻላል>>የሚል ዛቻ በየጊዜው በቴሌ ሰራተኞች ላይ እንደሚሰነዝሩ ታውቋል።በቅርቡ አንድ ሰራተኛ ቻይናውያን ጋር ተጣልተሃል ተብሎ ከስራ ሲባረር ሌሎች ደግሞ ከሀላፊነታቸው ዝቅ ተደርገው እንዲሰሩ መደረጋቸውን ለማወቅ ተችሏል።

## የግለሰቦች እንግልት ... (ከገጽ 1 የዞረ)

ነፍሰ በላው መለስ አንድም ጊዜ ከህዝብ ጋር ተቀላቅሎ ታይቶ የማያውቅ ሲሆን፤ ከአመታት በፊት አንድ የፓርላማ አባል <<መለስ በሱዳን ከአልበሽር ጋር በክፍት መኪና ለህዝቡ ሰላምታ እየሰጠ ስታልፍ ቴሌቪዥን አሳይቶህ ነበር። ለምድነው እዚህ እንደዚ የማታደርገው? አታውቀው እንደሆነ አንተ ወደ ቦሌ ስትሄድ እኛን መንገድ ላይ ካገኙን ወደ ውስጥ መንገድ አስገብተው ፊታችንን አዙረው ጠብመንጃ ይደግኑብናል።>> ብለው ሲናገሩ መለስ ፊቱ ጥላሸት ለብሶ እንዳዳመጣቸው እና መልስ መመለስ ተስኖት ግራ ተጋብቶ እንደነበር የሚታወስ ነው።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ ለውጥ አድርጓል።**

በዚሁ መሰረት ከአሁን ቦኋላ **በ7485 KHZ በ41 ሜትር ባንድ** እና **በ9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።